# የዘር ማፅዳት ዝግጅት በኢትዮጵያ

ብዙ ሰዎች ገና የፅሁፉን ርዕስ በመመልከት ሟርትርኛ ፣ ጥቁር ምላስ ወዘተ... የመሳሰሉትን አስተያየቶች ሊሰጡ ይችላሉ ፣ በኔ ግምት ግን እንደዚህ አይነት ግለሰቦች እውነታን መቀበል የተሳናቸውና በምናባዊ ዓለም መዋተትን እንደ ማምለጫና መሸሸጊያ የተጠቀሙ እውነትን ለመጋፈጥ የሞራል ብቃት ያልተላበሱ እራሳቸውን በማታለልና በመዋሸት የዕይታ አድማሳቸውን ያጠበቡ ልባቸው የተመኘውን እነሱ ስለተመኙት ብቻ እንደ ዕውነት ተቀብሎ መኖር ምርጫ ያደረጉ ስለሆኑ እነሱን ለማሳመን ሳይሆን ነገሮችን ሰፋ አድርጎ በተለያየ መንገድ ለመመርመርና ለመመልከት ፈቃደኛ ለሆኑ የተፃፈ ፅሁፍ ነው ።

እንደሚታወሰው ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ በወሎ ወልድያ የተናገረውን እዚህ ላይ ማንሳቱ የሂደቱን ጭብጥ መሰረት ያስይዛል ብዬ ስለማምን እጠቅሰዋለሁ ፣ በወልድያ ሟች ዶክተር አምባቸው መኮንን ፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ፣ ዶክተር ደብረፂዮን በተገኙበት ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ *ለክልሎች የምንሰጣቸውን ዓመታዊ ባጀት ክልሎች ልዩ ኃይልና ሚሊሺያ ያሰለጥኑበታል ያስታጥቁበታል* https://www.youtube.com/watch?v=iUWt9crrLqo በማለት ኮንኖ አክሎም *ከማንም በላይ የአማራው ብሄረተኝነት እንዳሰጋው ገልፆ ነበር*። ይህን በተናገረ በሳምንቱ በአማራው ክልል ከፍተኛ አመራር ላይ ያሉ ብርቅዬ የአማራ ልጆችን በመንግሥት ግልበጣ ሰበብ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቀነባባሪነት መስዋዕትነትን እንደተቀበሉና ከዚያ የግድያ ቀን ወዲህም እንዴት የአማራው ክልል ቁልቁል እየወረደ እንደሆነ ባይን የሚታይ በእጅ የሚዳሰስ ዕውነታ እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም ።

ይህ ከላይ የተጠቀሰው ግድያ ከመካሄዱ በፊት ግን የሆነ ነገር አለ ፣ ይሄውም የኦሮሞ የመስፋፋት ምኞት በወሎ ፣ በሰሜን ሸዋ ፣ በደራ እንዲሁም በቤንሻጉል ከሚያደርገው ትንኮሳ ባሻገር በተለይ በሰሜን ሸዋ በአጣዬ የአማራን መሬት ለመውረር የተደረገ ወረራ እንደነበር ይታወሳል ፣ ያንን ወረራ አማራው ተቋቁሞ ቢወጣውም ሆኖም ግን ይህንን ወረራ ያካሄደው ኦነግ ነው የሚል ወሬ ሲነዛ ነበር ። ሆኖም ግን ድርጊቱ በፌዴራል መንግስት የተመራ እንደሆነ ከበቂ በላይ ምልክቶች ስለነበሩ ምርመራ እንዲካሄድ ተጠይቆ የአማራው ክልል ከፍተኛ አማራሮች የሆኑና በሰኔ 15ቱ ግድያ የተፈጸመባቸው ያሰባሰቡት ያጣሪ ኮሚቴ አጣርተው እንደደረሱበት ወረራው ይመራ የነበረው በአብይ ሹመኛ በጄኔራል ብርሃኑ ጁላ መሆኑ ስለተደረሰበት ያንን ለማድበስበስና ደብዛውን ለማጥፋት መረጃውን ያጠናከሩትን አመራሮች በግድያ ማስወገድ ግድ ስለሆነ መንግሥት የሚያደርገውን አድርጎ በማይመስል ምክንያት የመንግሥት ግልበጣ ሊካሄድብኝ ነበር ብሎ አስደምሞናል ።

ከዚህ ሁሉ ድራማ በስተጀርባ ያለው ፍላጎት እንዳለ ሆኖ ፣ የአማራው ብሄረተኝነት ያሰጋው ጠቅላይ ሚኒስትር ፣ የክልሎች ልዩ ኃይልና ሚሊሺያን ማሰልጠንና ማስታጠቅ እጅግ የከነከነው ፣ ዛሬ እሱ የሚመራው *የኦሮሚያ ክልል ለ 30ኛ ጊዜ ልዩ ኃይልና ፖሊስ እንዳሰለጠነ በመንግሥታዊ መገናኛ መስመሮች አብስረውናል* ። ይታያችሁ አማራው ገና አንደኛ ዙር ስልጠና ሲያደርግ ያሰጋቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዛሬ በሚመሩት ክልል ለ30ኛ ጊዜ ያወገዙትን ልዩ ኃይል አሰልጥነው አስመርቀዋል ። ይህ ኃይል ባሁኑ ጊዜ ከ150,000 በላይ እንደሆነ ይነገራል ፣ ላንዱ ብሄር የተፈቀደው ለሌላው ያልተፈቀደው ለምንድነው? ብሎ ደፍሮ የሚጠይቅ ለአማራው ቆሜያለሁ የሚል ድርጅት አይደለም ግለሰብም ማግኘት አልተቻለም ።

እንደሚታወቀው የዘር ማፅዳት ወይንም ጭፍጨፋ ሊካሄድ የሚችለው መንግሥታዊ ስልጣን በያዘ ኃይል እንጂ ከመንግሥት ኃይል ውጪ ባሉና በተደራጁ የማሕበረሰብ ክፍሎች እንዳልሆነ ታሪክ ያስተምረናል ፣ ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የጀርመኑ “ሆሊኮስት” (Holocaust) በመባል የሚታወቀው የዘር ፍጅት አንዱ ሲሆን በጣም በቅርቡ ደግሞ በሩዋንዳ “ኢንተር ሃምዌይ” (Interahamwe ) በመባል የሚታወቀው የዘር ፍጅት የማንዘነጋው የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው ።

እዚህ ላይ የብዙዎች ሽውራራ እይታ ሊሆን የሚችለው የአብይ አስተዳደር በዚህ አይነት ድርጊት ሊሳተፍ እንደማይችልና አብይ ኢትዮጵያን አፍቃሪ መሪ ነው የሚል የተዛባ ግንዛቤ ያላቸው ቀላል የማይባል ቁጥር እንዳላቸው ይገባኛል ፣ ሆኖም ግን እነዚህ ግለሰቦች አንድም ከላይ በጠቀስኩት ምክንያት ምናባዊ ዓለም ላይ የሚኖሩ አሊያም ሌሎች በቀላሉ ሊያዩትና ሊገነዘቡት የቻሉትን መገንዘብ የተሳናቸው የዐይምሮ ዘገምትኞች ካልሆኑ በቀር ሁሉም እውነታ ከፊታችን ወለል ብሎ እየታየ አይተው እንዳላዩ ፣ ሰምተው እንዳልሰሙ ፣ አካባቢያቸውን ሳይሆን የውስጥ ስሜታቸውን ብቻ በማድመጥ የተጠመዱ ስለሆኑ እነሱን ማሳመን ቢያዳግትም እውነተኛ የማየትና የማስተዋል ክህሎት ላላቸው ግን እምብዛም የተሰወረ እንደማይሆን ይገመታል ።

ከሁሉም በፊት መረዳት የሚኖርብን ቁም ነገር በኦሮሞ ሥም የተደራጁ ማናቸውም የፖለቲካ ስብስቦች በቁጥር አስርም ይሁኑ ሃያ በመሃከላቸው ያለው ልዩነት *ስልጣኑን እኔ ልያዝ ፣ እኔ ልያዝ* ፣ እንጂ ቅንጣት ታክል የግብ ልዩነት የሌላቸው መሆኑን መረዳት ይሆናል ። ያንን ማመን ከተሳነን ፀሀይ ከምስራቅ ወጥታ ወደ ምዕራብ መጥለቋንም መጠራጠር ይኖርብናል ማለት ነው ። እነዚህ ስብስቦች ወያኔንም ጨምሮ ከጥንት አመሰረተታቸው አማራን እንደ ጨቋኝና ቅኝ ገዢ አድርጎ ስለአማራ በተከታዮቻቸው መሃከል የተዛባ ስነልቦና ቀርፆ ማደራጀት እነደነበር ይታወቃል ፣ ስለሆነም በዕቅዳቸው መሰረት አለመታከት ታሪክን አዛብቶ በማስተማር የተወሰነ ተሳክቶላቸዋል ማለት ይቻላል ።

የስልጣን እንጂ የግብ ልዩነት እንደሌላቸው በሺ የሚቆጠር ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል ፣ ከብዙ በጥቂቱ ለማስታወስ ያህል ታሪካዊው ኢትዮጵያ ጠሉ ኦነግ ከኤርትራ ከዘመናት ማንቀላፋት በኋላ አዲስ አበባ ገብቶ ትጥቁን ፈቶ በሰላማዊ መንገድ ሊታገል ነው ተብለን የነገሩንን የምንዘነጋው አይመስለኝም ፣ ይህ በንዲህ እንዳለ የቡድኑ መሪ ዳውድ ኢብሳ በሚዲያ ቀርቦ *ማነው ማንን ትጥቅ የሚያስፈታው* ብሎ እንቅጩን የነገረንን የሚዘነጋው ይኖራል ብዬ አላስብም ። ለኦነጎች በተደረገው የአቀባበል ስርዓት ላይም አዲስ አበባ ላይ የተጫነው ከንቲባ ታከለ ኡማ በሚገባን ቋንቋ ኦነጎችን *እንኳን ወደ አያቶቻችሁ ከተማ "ፊንፊኔ" በሰላም መጣችሁ* ብሎ አስደምሞናል ። በዚሁ አደባባይ ላይ ኦርቶዶክሳውያን ለዘመናት ሲያከብሩት የቆዩትን የመስቀል በዓል ያዋከበው አመራር ኢሬቻን ለመጀመሪያ ጊዜ ታሪካዊ ክብረ በዓሉ ከሚከበርበት ደብረዘይት ከሚገኘው የሆራ ሃይቅ ወደ መስቀል አደባባይ በመቀየር ሲያከብር *ነፍጠኛውን በሰበሩን በታ ሰብረናቸዋል* https://www.youtube.com/watch?v=Oqvhg2owoTw ሲል የኦሮሞ ክልል አስተዳዳሪ የሆነው ሽመልስ አብዲሳ በድጋሚ ወዴት እያመሩ እንደሆነ ጥርት ባለ ቋንቋ ነግሮናል ። ይህ ብቻም አይደል ጃዋር መሃመድ አዲስ አበቤዎች ለብዙ ዓመታት ቆጥበው ያሰሩትን የኮዬ ፈጬ የመኖሪያ ኮንዶሚኒየም ገጀራና አጣና ያነገቱ ጀሌዎችን በማሰባሰብ ለማንም እንደማይሰጥና የኦሮሞ ልጆች ሃብትና ንብረት እንደሆነ አስረግጦ በመናገር ዛሬ ያንን የተናገረውን አስፈፅሞ ተግባራዊ እንዳደረገው አይተናል ፣ በመንግሥትና በዓረብ ሐገራት እርዳታ ባቋቋመው ሚዲያ በተደጋጋሚ ፀብ አጫሪ ንግግሮችን ለጆሮ እስኪሰለች አስደምጦናል ፣ እንዲሁም አስቂኝ በሆነው ድራማው "ተከብቢያለሁ" በሚል ጥቃት የተሰነዘረበት በማስመሰል ባስነሳው አመፅ መንግሥት ባመነው ቁጥር ብቻ በትንሹ የ86 የንፁሃን ዜጎች ህይወት እንዲቀጠፍ ተደርጓል ። የወደመውንና የተዘረፈውን ንብረት ሳናካትት ይህን ሁሉ በደልና ግፍ በዜጎች ላይ አድርሷል በሚል አንድም ግለሰብ እስከ አሁኗ ሰዓት ድረስ በተጠያቂነት እንዳልቀረበ አስተውለናል ። በስልጣን ላይ ያለው አመራር ከሚናገረው በማር የተለወሰ ሬት ቃል ባሻገር በተጨባጭ በምድር ላይ ሲተገበር የምናየው ፀረ ኢትዮጵያዊነትና ፀረ አማራነት እንደሆነ ከማንም የተሰወረ ባይሆንም አውቆ ለተጨፈነ ግን ይህንን በዝርዝር ለማስረዳት አንደክምም ።

ታሪክ እራሱን ይደግማል የሚባለው እንዲያው ለማለት ያክል ሳይሆን እውነት ስለሆነ ነው ፣ ሰሞኑን በናዝሬት (አዳማ) ማርች 8 የሴቶች ቀንን በተመለከተ የኦፌኮ የወጣት ሴቶች አደረጃጀት ውስጥ የምትሰራ

አንዷት እድገቷ ኦነጋዊ የሆነችና አስተሳሰቧ በፅንፈኞች አማራና ኢትዮጵያ ጠል ትርክት የተዘባበት ወጣት በስብሰበው ላይ ተነስታ ፍፁም ጥላቻን ባዘለ አነጋገር *"ኦሮሞ ሆናችሁ ነፍጠኛ (አማራ) ጋር የተጋባችሁ ተፋቱ"* ፣ https://www.youtube.com/watch?v=6tQ7QuuufmM በማለት ለራሷም ምኞት ማስታወቂያ መሰል በመስራት ሚስቶቻችሁን ፈታችሁ እኔንም ማግባት ትችላላችሁ እንደኔም ባል ያጡ ብዙ ቆነጃጅት የኦሮሞ ወጣት ሴቶች አሉ በማለት ስትዘላብድ ሰምተናል ። ይህ አባባል ለኛ በጣም ትንሽ ሊመስለን ይችል ይሆናል ነገር ግን አይደለም ፣ ከላይ እንደተጠቀሰው ታሪክ እራሱን ሲደግም እያየን እንጂ ፣ ይህን መሰል መልዕክት በሩዋንዳ የዘር ፍጅቱ ከመካሄዱ በፊት በየሚዲያው ይለፈፍ የነበረው ዛሬ ከምንሰማው መልዕክት ጋር ተመሳሳይ ነበር ፣ ዲቃላም የሚለው ከዚሁ ከሩዋንዳው ፍጅት (Interahamwe) ጋር ተመሳሳይ ብቻ ሳይሆን አንድ አይነት ነው ፣ በሩዋንዳ ውስጥ ዲቃላ የሚሏቸውን *ከሁቱና ከቱሲ* የተጋቡና የተወለዱት ነበሩ ፣ እነሱም ናቸው የመጀመሪያ ሰለባ እንደነበሩ የትላንት ታሪካቸው የሚነግረን ። ይህ ተመሳሳይ ሰቆቃ በኢትዮጵያ ሊፈጸም አይችልም ብሎ ማሰብ ሲበዛ የዋህነት ይሆናል ። አረቦች ሲተርቱ *"አላህን እመን ግን ግመልህን ማሰር አትዘንጋ ይላሉ"* ፣ በኛም ሐገር አባባል *"አይመጣምን ትተሽ የመጣልን ባሰብሽ"* የሚል የአበው አባባል እንዳለን የማያውቅ አለ ብዬ አላምንምና ነገሩን አፅንዖት ሰጥቶ መመርመሩ ይጠቅማል እንጂ አይጎዳም ።

እዚህ ላይ መረዳት የሚኖርብን ነገር ቢኖር የዚች ወጣት አነጋገር እና እሳቤ ድንገተኛ እንዳልሆነና ለዘመናት በትጋት ሲሰራበት የነበረ የፅንፈኞች የስራ ውጤት እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል ። በብዙዎች ዘንድ እንደ አስቂኝ እና አዝናኝ የሚቆጠሩት ፕሮፌሰር መራራ ጉዲና ከዓመታት በፊት *ቀን ቀን አማራን እያወገዙ ማታ ማታ አማራ ሚስታቸውን አቅፈው ያድራሉ* ያሉት እንዲያው ለማሳቅ ሳይሆን ከልብ የሚከነክናቸውን ፣ የሚያማቸውንና የሚቆጠቁጣቸውን አውጥተው መናገራቸው እንደሆነ ያስተዋለ ይኖራል ብዬ አላምንም ።

ትላንት አማራው ከወያኔ እስር ቤት እንዲፈቱ የጮኸላቸው አቶ በቀለ ገርባም ትክክለኛ ማንነታቸውን በማሳየት ፣ ሰልፋቸውን በማስተካከል አሁን ለውጥ ተብዬው ከመጣ በኋላ *አማርኛ እንዳታወሩ ፣ ከአማራ ጋር እንዳትገበያዩ* https://www.youtube.com/watch?v=_JMTHI67uXE ያሉትና መሰል የጥላቻ ንግግሮችም ወፍ ዘራሽ ሳይሆኑ መሰረታዊ የአደረጃጀታቸው የመሰረት ድንጋይ የሆነውን እምነታቸውን ነበር የነገሩን ። በነዚህ ብቻ አያበቃም ነውጠኛውና በጥላቻ የሰከረው ጃዋር መሐመድም *አንገቱን በሜንጫ ነው የምንለው* ከሚለው ንግግሩ ባሻገር በሰፊው የሚታወቅበት ኢትዮጵያና አማራ ጠል ንግግሩ ገና እግሩን ወደ ኢትዮጵያ ሳያስገባ በፊት ያራምድ የነበረው መርህ *ኢትዮጵያ (አማራ) ከኦሮሞ ምድር ትውጣ (ይውጣ) (Ethiopia out of Oromia)* https://www.youtube.com/watch?v=uXah_qtW8sg የሚለው የጥላቻ መንገድ በሰፊው የሚታወቅበት የማሰባሰቢያና የማደራጃ መፈክሩ እንደሆነ ዓለም ያወቀው ፀሀይ የሞቀው እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም ። ከላይ የተጠቀሰው የኦሮሚያ ምክትል አስተዳዳሪ ሽመልስ አብዲሳ በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ላይ የኢሬቻ በዓል በሚከበርበት ወቅት *ነፍጠኞችን (አማራን) በሰበሩን ቦታ ሰበርናቸው* ብሎ የተናገረው ሌላኛው ማስረጃ ይሆናል ። እንግዲህ ከብዙ በጥቂቱ የኦሮሞ አደረጃጀት ዋና መሰረቱ አማራ ጠል መሆኑ ሁሉንም ድርጅቶች በአንድነት የሚያስተሳስራቸው ሲሆን ሌላኛው አንድ የሚያደርጋቸው ደግሞ *አማራ ማለት "ኢትዮጵያ" ፣ ኢትዮጵያ ማለት "አማራ"ማለት እንደሆነ አድርገው የሳሉት የተንሻፈፈ ግንዛቤ ይሆናል ፣* በማከልም የሐገራችን የብዙ ዘመን መለያ የሆነው *ሰንደቅ አላማችን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ* የሆነውን ሁሉም በጋራ የሚስማሙበት ኢትዮጵያዊ ወይንም አማራዊ መለዮ አድርጎ በመቁጠር ሊያዩትና ሊሰሙት አለመፈለጋቸው ይሆናል ። ከዚህ ውጪ ማናቸውም የኦሮሞ ድርጅቶች ማን ይምራ ፣ ወይንም ማን ይግዛ እንጂ የግብ ልዩነት የሌላቸው እንደሆነ የተመሰከረለት ያደባባይ ሚስጥር ነው ።

ወደተነሳሁበት ቁም ነገር ስመለስ የዘር ፍጅት በኢትዮጵያ ሊመጣ እያንዣበበ እንደሆነ ለማንም ግልፅ ነው ፣ ይህም የዘር ፍጅት የሚሆነው በቀዳሚነት በአማራው ላይ ሊሆን እንደሚችል አጠያያቂ አይሆንም ፣ አካሄዱ

ጠቋሚ ነውና ። አሁን በጣም በተደራጀ ሁኔታ የታጠቀው ሁለት ቡድን ማለትም ኦነጋዊው ኦሮሞና የትግሬው ወያኔ ሁለቱም ሲመሰረቱ ጠላት አድርገው በማኒፌስቷቸው ላይ ያሰፈሩት ቁጥር አንድ ጠላት አማራ መሆኑን አንዘንጋ ፣ አሁንም ሁለቱም ድርጅቶች የአማራውን ግዛት እየተጋፉና ግዛታቸውን እያስፋፉ እንደሆነ እያየነው ነው ፣ ሁለቱም በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰራዊት አደራጅተውና አስታጥቀው ነገር ግን አማራውን እንዳይደራጅና እንዳይታጠቅ አድርገው በባዶ እጁ ያቺን ጎዶሎ ቀን እንዲጠብቅ በተቀነባበረ ሁኔታ እየደገሱለት እንደሆነ የማንክደው የዘመናችን ክስተት ሊሆን ቀኑን እየቆጠረ (እየጠበቀ) እንዳለ ማየት የተሳነው ካለ እጅግ ያሳዝናል ። በዕውነት የኔ አመለካከትና ግንዛቤ ስህተት ከሆነ እኔም ምኞቴ አማራው ላይ ግፍ ሲፈፀም ማየት ስላልሆነ ስህተት ብሆን እመርጣለሁ ። ነገር ግን ከምናየውና ከምንሰማው ተጨባጭ ሁኔታዎች አንፃር ስንነሳ ግን በዕውነት በግንዛቤዬ የተሳሳትኩ አይመስለኝም ።

ትላንትን እየዘነጋን ዛሬን ማየት ከተሳነን ሊመጣ ያለን ለመተንበይ እንዴት ይቻለናል? እስኪ ባለፉት አንድ ዓመት ተኩል የተፈፀሙትን ድርጊቶች እራሳችንን በመጠየቅ ወደኋላ እንቃኘው ። ትላንት አይደለም እንዴ በቡራዩ ፣ በሲዳሞ ፣ በሐረር ፣ ጭፍጨፋ የተካሄደው? ትላንት አይደለም እንዴ ከ45 በላይ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተቃጠለውና ምዕመናኑ በግፍና በጭካኔ የታረዱት? ትላንት አይደለም እንዴ ለወደፊት በአማራው ላይ ሊፈፅሙትና ሊያከናውኑት ያቀዱትን በአደባባይ ወጥተው በድፍረትና በማን አለብኝነት የነገሩን? https://www.youtube.com/watch?v=xA0yKEpzgbI በየጊዜው በተለያዩ ስፍራዎች የተፈናቀለውስ አማራ? በሚሊዮን የሚቆጠር የጌዲዮ ተፈናቃይስ? በጠቅላላ በሐገሪቱ ከ3 ሚሊዮን በላይ የተፈናቀለውስ ዜጋ? የተቆረጠውስ ጡት? በቅርቡ አነጋጋሪ የሆነው የ21 የአማራ ወጣት ልጃገረዶች መታፈንና ደብዛ መጥፋትስ ? ይህን ሁሉ ግፍና መከራ የዓለም ሚዲያዎች ዘገቡት? አልዘገቡትም! ምክንያቱም ዛሬም ታሪክ እራሱን ይደግማል እንዳልነው በሩዋንዳም የዘር ማፅዳት አደጋ እያንዣበበ ባለበት ወቅት ሁኔታው ያስፈራቸው ለዓለም መንግሥታት ቢያሳስቡም ልክ ዛሬ በኛ ሐገር ላይ እንደሚፈፀመው ሁሉ ድርጊቱ ከመፈፀሙ በፊት የዓለም ሕዝብ እንዳያውቀው አፈና ተደርጎ እንደነበር ታሪክ መዝግቦ አስቀምጦልናል ።

ከላይ እንደተጠቀሰው የዘር ማፅዳት ወይንም ጭፍጨፋ ሁሌም መንግሥት መራሽ እንጂ በግለሰቦች ወይንም በተደራጁ ቡድኖች የሚፈፀም እንዳልሆነ ከታሪክ የተማርነው ስለሆነ አሁን በኦሮሚያ ፅንፈኞች የሚደረገውም የኦነግ ፣ የኦዴፓ ፣ የኦፌኮ ወዘተ ሳይሆን በመቀናጀ የሚተገበርና መንግሥት መራሽ እንደሆነ መቀበልና ማመን የግድ ይላል ። ፅንፈኞቹ የስልጣን እንጂ የግብ ልዩነት የሌላቸው ፣ ያንድ ሳንቲም ሁለት ገፆች መሆናቸውን አምነን መቀበል ይኖርብናል ፣ ኦሮሚያን የሚመራው ሽመልስ አብዲሳ ሳይሆን አብይ አሕመድ እንደሆነ ማመን ግድ ነው ፣ ሽመልስ የኦሮሚያ *ምክትል* አስተዳዳሪ እንጂ ዋና አስተዳዳሪ አይደለምና በተመሳሳይ የአማራው አስተዳዳሪ ተመስገን ወርቅነህ ሳይሆን ደመቀ መኮንን እንደሆነ ሁሉ ፣ ስለሆነም ኦሮሚያን ለ30ኛ ዙር አሰልጥኖና አስታጥቆ በአማራው ላይ ለመዝመት የመዘጋጀቱን ሂደት ቀዳሚ መሪው *አብይ አሕመድ* እንደሆነ ማመንና መቀበል ይኖርብናል ። የዘመቻውም መሪ እሱው አራሱ ሆኖ በሰኔ 15ቱ ወታደራዊ ፋቲጉን ለብሶ https://www.youtube.com/watch?v=RVMMyShLAfM እንዳሳየን ሁሉ የጦር ኃይሎች አዛዥ አብይ አህመድን በተመሳሳይ ሁኔታ የምናይበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም ። ስለሆነም የዘር ማፅዳት ዝግጅት በኢትዮጵያ አይቀሬነቱን አውቀን በጊዜ ብንዘጋጅ ፣ መምጣቱን ማስቀረት ባይቻልም እንኳን የጥፋቱን መጠን ግን በእጅጉ መቀነስ ይቻላል ብዬ አምናለሁ ።

እግዚአብሐር ኢትዮጵያን ይባርክ

ታዛቢው

March 13, 2020